# ኢየሱስ፣ ቴዎድሮስ፣ ብርቱካን = ሶስት ህማማት

ተጻፈ በዕለተ ሆሳዕና 2001 ዓ. ም.
ሙሉነህ ዮሃንስ-ከሲያትል

በእለተ ሰንበት በአለ ሆሳዕናን ለማክበር እንድችል ከወትሮው ቀደም ብየ ወደ አልጋየ ተከተትኩ። ነገር ግን እንቅልፍ እምብኝ አለኝ። በቀኝ ጎኔ-በግራ በኩል-በጀርባየም ሞከርኩት። እንቅልፍ እርቆኛል። እኩለ ሌሊት ካለፈ ሶስት ሰዓታት ነጉደዋል። በሃሳብ ስጉላላ አንሶላየን እየገለጥኩ የትራስጌ መብራት ሶስት ጊዜ አበራሁ። አዎን እዳ ተሸክሞ መተኛት ከበደኝ። ሸክሜን ለማቅለል ሃሳቤን በወረቀት ጠቅጥቄ ለናንተው አስተላለፍኩ። እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቻችሁ ትጋሩኛላችሁ፤ ባይሆንም አንድየ ይስማኝ።

ይህ ጽሁፍ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጭካኔ በተሰቀለ በ1971ኛው ዓመቱ፣ አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ በተሰዋ በ141ኛው ዓመቱ እንዲሁም ብርቱካን ሚደቅሳ በጭካኔ በታሰረች በ104ኛው ቀን ተጻፈ። ሶስቱን ስሞች በአንድነት ተደርድረው ስታዩአቸው ጥያቄ ወይንም አግራሞት ፈጥረውባቹህ ይሆናል። ስሞቹን ግን ለንፅፅር እንጂ ለማወዳደር አላመጣሁም-አይቻልምም-አይገባም። ነገር ግን አሁን ያለንበት ወራት እንዲጋሩት የሚያደርጉ አበይት ከባባድ ቁም ነገሮች አሉ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር የአብይ ጾም መጨረሻ ሳምንት ሰሞነ ህማማት ይባላል። ወደኋላም ለየብቻ ለማብራራት እማክራለሁ።

በቅድሚያ ግን ከዚህ ቀጥሎ የምዘረዝራቸውን ጉልህ ነጥቦች ልብ በሉልኝ፦ **ለድህነት መምጣት፣ መስዋዕትነት፣ በራስ ወገን አሳልፎ መሰጠት፣ ያለወንጀል መፈረድ፣ በጠላት እጅግ መፈራት፣ ህዝብን ወደተስፋ ምድር ማሸጋገር፣ በታሪክ ስምን ማስጠራት።** እነዚህን አበይት ቁምነገሮች በመውሰድ ለአርዕስትነት የተጠቀምኩበትን ሶስት ህማማቶች አንድ ባንድ እንይ።

<u>**የክርስቶስ ሕማም**</u>፦ በክርስትና ህይወት ያላችሁ እንደምታውቁት ያለ እንከን የተፈጠረና ገነት መኖሪያው ሆና የተሰጠችው የሰው ልጅ ብቸኛዋን የአምላክ ትዕዛዝ ጥሶ ለአምስት ሽህ አምስት መቶ አመት የፍዳን ዘመን አሳለፈ። የሰው ክፋት ማለቂያ ባይኖረውም እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ወደደ። ጌታ ክርስቶስ ከእመቤታችን ተወልዶ ሰውን ለማዳን እስኪሰቀል ድረስ ያለውን የመጽሃፍ ታሪክ ስናይ ሊያድናቸው በመጣላቸው ወገኖች እጅ የተቀበለውን ስቃይና መከራ ለመግለጽ እጅግ ይከብዳል። የመጨረሻዋን የህማማት ሳምንት ለማሳለፍ ኢየሩሳሌም ከተማ ጉብታ ላይ ሲደርስ ለከተማዋ እጅግ አዘነላት አምርሮም አለቀሰላት በሃጥያት ጨቅይታ ነበርና። ከህማማቸው ሲፈውሳቸው የነበሩት ወገኖቹ ግን ክርስቶስን ለመግደል በሃሰት ወነጅሉት፤ ይልቁንም እስራኤልን በባርነት ይገዛቸው ለነበረው ለቄሳር አገዛዝ አሳልፈው ሰጡት። ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ስቀለው-ስቀለው አሉት። ፍቅሩ ተወዳዳሪ የሌለው ክርስቶስ ግን በሱ መስዋእትነት የሰው ልጅ እንዲድን ከፊትም ፈቅዶ ነበርና እራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ የአዳም ዘርም ዳነ።

<u>**የአፄ ቴዎድሮስ ሕማም**</u>፦ የመይሳውን ታሪክ ከሰሞነ ህማማት ጋር ያያዝኩት እንዲሁ አይደለም። አባታጠቅ በተወለደ በ50 ዓመቱ በወርሃ ሚያዝያ በሰሞነ ህማማት መግቢያ በሆነችው በእለተ ሆሳእና ነበር መቅደላ አምባ ላይ የጀግና ሞት የሞተው። ወጣት

ካሳ ሃይሉ አገር አማን ብሎ በሚማርበት በታላቁ የማህበረ ስላሴ ገዳም (አሁን ባለው አገዛዝ ወደሱዳን እንዲሰጥ ከተወሰነባቸው ቦታዎች አንዱ) ውስጥ ኢትዮጵያን ተቀራምተው ከያዟት የዘመነ መሳፍንት ገዥዎች አንዱ ሰራዊቱን አዝምቶ አያሌ የገዳማቱን ንጹሃን ጨፈጨፈ። በተፈጸመው ግፍ እጅጉን ያዘነው ወጣቱ ካሳ ሃይሉ ከገዳሙ በመሸሽ በቋራ በርሃ የነጻነትን ትግል ጀመረ። ግፍ የወለዳቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች ከየማእዘናቱ በመሄድ የካሳን ጦር ተቀላቀሉ። በየጠቅላይ ግዛቱ ታናናሽ ዘውዶችን በራሳቸው ላይ ጭነው ኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስት ያሳጧትን መሳፍንቶች ታሪክ ጸሃፊዎችን በሚያስደምም ፍጥነት የቋራው አንበሳ ጠራረጋቸው፤ የዘመናዊት ኢትዮጵያን ምስረታ ስሜን በምትገኘው ደረስጌ ማርያም አበሰረ።

ከአንዱ ጠቅላይ ግዛት ወደ ሌላው ከነሰራዊታቸው እየተንከራተቱ ኢትዮጵያን ያቀኗት አፄ ቴዎድሮስ ለጠላት አመቻችቶ የሰጣቸው ግን የገዛ ወገን ነው። ኢትዮጵያን በመቀራመት ይበዙብዙ የነበሩ የዘመነ መሳፍንት ቅሪቶችና አፍቃሪዎች ታናናሽ ዘውዶችን በጉያቸው ሸጉጠው በንጉሱ ላይ ተደጋጋሚ አመጻዎች አደረጉ። ድካማቸውንም አበዙ። ጉዞው የእግር እንደነበር አንባቢያን እንዳትዘነጉ። ከሚቃጣባት ተደጋጋሚ የውጭ ወራሪ ጥቃት እራሷን መከላከል የምትችል ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጥረት ካልወደደቸውና ትብብር ከነፈገችው የእንግሊዝ መንግስት ጋር ወደ ጠርነት ተገባ። በጊዜው በዘመናዊ ተደራጅቶ ለመጣው ለጄኔራል ናፒየር ጦር መንገድ ጠራጊ በመሆን በሃገራቸውና በህዝባቸው ላይ ደባ የፈጸሙት ወገን የሆኑት ኢትዮጵያውያን ነበሩ። እንደክርስቶስ መይሳውንም የገዛ ወገኖቹ ለጠላት አሳልፈው ሰጡት። ንጉሱ የሚወዳቸው ሁሉ አንድ በአንድ በክብር አለፉበት። የጀግንነትና የታማኝነት መለኪያው ገብርየም ለነጻነት የጥይት አሩር ተቀበለ። የአብራኩ ክፋይ የሆነው ወጣቱ አለማየሁ ያለአባት እየቀረ እንደሆነ ታወቀው። ከሁሉ አብልጠ የሚወዳት ኢትዮጵያ በጠላት መደፈሯን ማየት አልፈቀደም። እናም በዛ የጭንቅ ሰአት ልትውልድ የሚተላለፍ ታላቅ መስዋእትነት ፈጸመ። ለራሱም-ለህዝቡም-ለሃገሩም የጀግንነት ሞት ሞተ። ትውልድም ታሪኩን ወርሶ አያሌዎች በስሙ ተጠሩ አያሌዎች ወኔውን ተላብሰው ለሃገር ደህንነት መስዋእት ሆኑ። ታላቁ መሪ በአለ ፋሲካን ሳያይ በህማማት ሰሞን ነበር የተሰዋው። እኔም በየአመቱ ህማማት ሲደርስ የጌታ ክርስቶስን ስቃይ ሳስብ የአባ ታጠቅንም እንዲሁ አስታውሳለሁ። ነፍስ የማርልኝ።

<u>የብርቱካን ሕማም</u>፦ ብርቱካን ወካይ ናት። እናትነትን፣ እህትነትን፣ እሴትነትን፣ ወጣትነትን ትወክላለች። እንደሷም በግፍ የታሰሩ አያሌ ወገኖቻችን ተምሳሌ ናት። ብዙ ህጻናት ስማቸው በብርቱካን እንደሚሰየም እገምታለሁ። እዚህ ባለሁበት አገረ አሜሪካ የነጻነት ምልክታቸው ኒው ዮርክ ከተማ በክብር ከፍ ብላ ሃውልት የተሰራላት ሴት ናት። ፈረንሳይ ሃገርም ከሄዳችሁ ፓሪስ ከተማ ከሚገኘው ከታላቁ የኤፍል ማማ ጎን ለጎን የቆመችው የነጻነት ሃውልት ሴት ናት የአርበኝነታቸው መለኪያም ጃን ደ አርክ ናት። ወደ ራሳችን ጉዳይ ወደ በርቱዋ የዘመናችን ወጣት አርበኛ ልመለስ።

ታዲያ አጀማመሬ ላይ እንደነገርኳችሁ እንቅልፌን እንዳልተኛ ያደረገኝ ዋና ምክንያት በእኛም ዘመን ታሪክ እራሱን እየደገመ ወቅቱ የሚጠይቀን የኢትዮጵያዊነት እዳ ስላለ ነው። ለህዝብና ለሃገር ደንታ የሌላቸው ያሁኑ የኢትዮጵያ ገዥዎችም የነጻነት ተምሳሌታችን የሆነችውን ንጹህ ሰው የሃሰት ወንጀል ወንጅለው እድሜዋን በሙሉ በእስር

እንድትማቅቅ በአንድ ጠባብ ክፍል አጉረዋታል። አዎን ስለብርቱካን ሚደቅሳ ነው የምብሰለሰለው። አያሌ ኢትዮጵያዉያንም ብርቱዋን እንደሚያስቡ አውቃለሁ። ነገር ግን ከባዱን ጥያቄ እንጠይቅ፤ የነጻነታችን ተምሳሌት አድርገን የምናያትን እህታችንን ለማስፈታት ምን አደረግን? ለመሆኑ በዝምታችንስ አሳልፈን አልሰጠናትም? በታሪክ አጋጣሚ እዚሁ ወዳለሁበት የሲያትል ከተማ ከሁለት አመት በፊት ብርቱካን መጥታ ነበር። ለፍትህ ለነጻነትና ለእውነት ጥልቅ አመለካከት ያላት፤ ለወገኗ በፍቅር የምትችለውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጣ የተነሳች እንደነበረች ለመገንዘብ እድሉ ገጥሞኛል። የገዥው ቡድን የብርቱካንን አመራር እጅጉን ስለፈራው በሃሰት ወነጀላት። ክርስቶስ ክስ ተመስርቶበት ወደፍርድ ሲያቀርቡት ከሳሾቹን ቸግሯቸው የነበረው አብይ ነገር ምን ብለው እንደሚከሱት ነበር። ምክንያቱም ከደግነትና ከማዳን በቀር አንዳችም የተገኘበት ስህተት አልነበረምና። ወገኖቹ ግን ድምጻቸውን አስረዝመው ኢየሱስን እሰር ነፈሰ ገዳዮን በርባንን ደግሞ ከእስር ፍታልን በማለት ጮሁ።

አሁንም ወንጀለኞች አራት ኪሎ ተቀምጠው በንጹኋ ብርቱካን ላይ ፈረዱ እንደ በርባን የሰው ደም የሚጠየቅበትን የሽፍትነት ጓደኛቸውን በምትክ ፈቱ። ህማማተ ሰሞን ከባድ ድባብ አለው። ክርስቶስ ከዳርቻዋ ሆኖ ለኢየሩሳሌም እንዳለቀሰላት እንጦጦ ጋራ ላይ ሆነው አዲስ አበባን ቁልቁል ቢያዩዋት ምንአልባትም የበለጠ የሚለቀስላት ሳትሆን አትቀርም። ቁጥሩ ቀላል ይመስል በሚሊዮን የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ወገን የሚበላው የሚጠጣው አጥቶ ያለማቋረጥ በየአመቱ ለልመና ይዳረጋል። የነመለስ የንግድ ድርጅቶች ግን የዚሁን ደሃ ህዝብ ሃብት እየዘረፉ ከአይኑ ስር ንግድ ይነግዱበታል፣ በርሃብተኛውም ስም የሚመጣውን ምጽዋት ወደ ካዝናቸው ይሰንቃሉ(መቼ ሊበሉት-እንዴትስ ሊበሉት ይሆን!)፣ ለመቁጠር የሚያቅት ብር እያሸሹ እንደሚገኙ ገንዘባቸውን የሚደብቁላቸው የውጭ አገር መረጃዎች ሳይቀር ያጋልጣሉ። ይህን ሁሉ ግፍ አይቶ እንዳላየ ሆኖ የሚኖረው፤ እባክህ ልኑርበት የሚለው ወገን ብዙ ነው። እንደጴጥሮስም ብርቱካንንና የቆመችለትን አላማ የሚክደውን ቤቱ ይቁጠረው። አቤት ህማም። አንጻራዊ ነጻነት ባለበት ሃገር ሆኜ ስለሆነ ሃሳቤን የምጽፈው፤ አንዳንድ ነገሬ ትዝብት ላይ ሊጥለኝ ይችላል። አሁን ኢትዮጵያ ብኖር ምን የተለየ እንደማደርግ አላውቅም። ነገር ገን እዚህም ሆኜ የማስበውን መተንፈሴ አይቀርም። እናም እናንተ ኢትዮጵያውያኖች ብርቱካንን ለማስፈታት ምን አደረጋችሁ? የማትችሉትን ሳይሆን የምትችሉትን እንኳ ምን እንዳደረጋችሁ? ውስጣችሁን ጠይቁ። የምትመራው የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ደጋግመው ጮኸት እያሰሙ ነው። ነገር ግን ህዝቡ በዚህ ጉዳይ አብሯቸው እንዲሰለፍ በቂ ያደረጉ አይመስለኝም። በአንድ ቅጥር ጊቢ በወር አንዴ ብቻ የብርቱካንን ስም ማሞገስ ከእስር የሚያስወጣ በቂ ትግል አይምስለኝም። የሰው ቁጥር በጣት ተለክቶ ሰልፍ እንዲወጣ መጠየቅ አንጀት አያርስም። ያንኑም ተከለከሉ። <u>ስግደትንና ፋሲካውን የምታከብሩ የአንድነት ሰዎች እስቲ በአንድ ቤተክርስቲያን በአንድነት ተገኝታችሁ በህዝባችሁ በሃል ሆናችሁ ጸልዩ። እስላም ወገኖችም እንዲሁ።</u> ትችቴ ግን በገንቢ እንደሚታይ ተስፋ አደርጋለሁ። አንባቢዎች ሽክሜን እያቀለልኩ ነው። ለብርቱካን ጸልዩ፣ ለሃገራችን ጸልዩ፣ ለህዝባችን ጸልዩ። አዎን ፈቃዳችሁ የሆነ ጌታ ክርስቶስን በህማሙ እንደምናስብ ፋሲካን ለማየት ላልታደለው ለአባ ታጠቅና መሰል ጀግኖቻችን ነፍስ ይማር በሉ። ብርቱካን

**ከአዳኞቿ እጅ ወጥታ ከምትወዳቸው ልጇና እናቷ እንድትቀላቀል ተግታችሁ ጸልዮ። ይህ የመለስን ፈቃድ አይጠይቅምና። ኢትዮጵያችን እስላምና ክርስቲያኑ በፍቅር የሚኖርባት ናትና ጥላቻን ከሚዘሩ እንጠንቀቅ።**

**ስደመድም እንዲህ ነው። ነጻነት እና ድህነት ሁሌም ዋጋ ይከፈልበታል። የአገዛዙ አለቃ የሆነው ሰውዮ ብርቱካንን እንዴት እንደሚፈራት ይገርማል። ስሟን ጭምር ነው የሚፈራው። ስለብርቱዋ ሲነሳበት እየተንቀጠቀጠ "ሴትዮዋ" እያለ ነው የሚጠራት። እህታችን ብርቱካን የእኛን የነጻነት ዋጋ እየከፈለች እንደሆነ የማውቀውን ተናግሬ ላብቃ። እነመለስ ሊያስሯት ሁለት ቀን ሲቀር ውጭ ያለን ኢትዮጵያውያን በብዛት ስልክ እየደወልን ሁኔታውን እንከታተል አስተያየትም እንለዋወጥ ነበር። እናም እኔም እድል አግኝቸ ለብርቱየ ደወልኩላት። መጀመሪያ ቀለል ባለ ስሜት እየሳቀች አዋራችኝና እኔስ ምን አስተያየት እንዳለኝ ጠየቀችኝ። አደዋወሌ የሰላምታ መሆኑን ገልጬ በርች ስላት በእረኸሙ ሰቃ እኔማ ምክሩ ጎርፎ ተራራ ስላከለ ምን ትጨምር ይሆን ብየ ነው በማለት በዛ ከባድ ሁኔታ እንኳን ከውስጤ የሚነበብኝን የኔን ሃሳብ ልታቀልልኝ ሞከረች። በጣም ገረመኝ። በመጨረሻም በጭንቅላቴ አሁንም የሚያቃጭለውን ውሳኔዋን ነገረችኝ። ብርቱካን እንዲህ አለች"ወሳኔዮ እውነትን መናገር ነው። በጽሁፍ አሰፍረዋለሁ። በፍርሃት ለባለስልጣናት አላጎበድድም። የቆምኩለት አላማየን አላጥፍም። ይህን ባላደርግ ህሊናየስ ሕዝቤስ ምን ይላል"።**

አምላክ ኢትዮጵያን ይባርክ::

አስትያየት ካላችሁ:- muleur@yahoo.com